**ከአውሮፓ የአማራ ማህበራት ፌደሬሽን የተሰጠ መግለጫ**

## ከወደቁ በኋላ መንፈራገጥ ለመላላጥ !!!

ሰሞኑን በቪዲዮ እየተሰራጨ ባለዉ በሰሜን ሸዋ ደራ ወረዳ ላይ የተፈጸመ አሰቃቂ ወንጀል በግፍ ለተገደለው ወጣት ፌደሬሽናችን የተሰማዉን ጥልቅ ሃዘን እየገለጸ ይህንንም ተከትሎ የብልጽግና አገዛዝ በስፋት የተያያዘዉን የእርስ በእርስ እልቂት ሊያመጣ የሚችል የሚዲያ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ፌደሬሽናችን በጥብቅ ያወግዛል፡፡

የተለያዩ ተዓማኒነት ያላቸው መረጃዎች እንዳረጋገጡት ፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ህይወቱን የተነጠቀው ወጣት አገዛዙ በሚስጥር ባደራጃቸው ስኳድና አጥፊ ሃይሎች አማካኝነት ሲሆን በብሄሩም የአማራ ተወላጅ ከመሆኑም በላይ በቂ መረጃ ባልተሰባሰበበት ሁኔታ የአገዛዙ ባለስልጣናት በሩጫ ወንጀሉን የፈጸመው ፋኖ እንደሆነ አድርገው ማቅረባቸው ወንጀሉ በአገዛዙ አቀነባባሪነት የተፈጸመ ስለመሆኑ አመላካች መረጃ ነው። ከዚህም ባለፈ ወንጀሉ የተፈጸመው ቀደም ብሎ የኦሮሞ ልዩ ሃይሎች ተደጋጋሚ ወንጀል በፈጽሙበት አካባቢ በመሆኑ ድርጊቱ በተቀነባበረ መልኩ የተከናወነና በአማራና ኦሮሞ ህዝቦች መካከል እልቂትን ሊያስከትል የሚችል ግጭት እንዲፈጠር ለማድረግ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ነው ።

አገዛዙ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት ወንጀሉን የፈጸመው ፋኖ ነው በሚል ያቀረበው የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ፍጹም ተቀባይነት የሌለውና የሚወገዝ ሃላፊነት የጎደለው አካል እኩይ ሴራ መሆኑ ጥያቄን የሚያስነሳ ካለመሆኑም በላይ፣ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የፋኖ ሃይሎች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ከሥርዓቱ ጋር በነበሩ የውጊያ ግንባሮች በምርኮ የተያዙ የአገዛዙ ሠራዊት አባላት የሆኑ የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የጋምቤላ እና ሌሎችም ብሔረሰብ ተወላጆች ሰብዓዊ ክብራቸው ተጠብቆላቸው በክብር ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲገናኙ እየተደረገ ባለበት ሁኔታ አገዛዙ የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም እያሰራጫቸው ያሉ የሃሰት ውንጀላዎች ተቀባይነት የላቸዉም፣ ሊኖራቸውም አይችልም ።

ባለፉት 6 ዓመታት ተመሳሳይ የሆኑ አስነዋሪና አሰቃቂ ማንነትን መሰረት ያደረጉ  ሰውን ከማረድ በሕይወት እስከ ማቃጠል፣ ንጹሐንን ዘቅዝቆ ከመስቀል አስከሬንን በመኪና እስከ መጎተት፣ በዱላ ቀጥቅጦ ገድሎ በጅምላ እስከ መቅበር፣ ከብልትና ጡት መቁረጥ አስከ የነፍሰ ጡር ሆድ ቀዶ ሽልን እስከ መጣል የዘለቁ ዘግናኝ እኩይ ሥራዎች ሲፈጸሙ የቆዩ መሆናቸው በማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በግልጽ ይታወቃል ። እንዲህ ያለው ተግባር ተቋማዊና በተጠና መልኩ ትናንት የተፈጸመ፣  ዛሬም እየተፈጸመ ያለ አገዛዙ እስካልተወገደ ድረስ  ወደፊትም የሚቀጥል ነው ።  ከዚሁ ጋር ተያይዞ እውነታው ይህ ሆኖ እያለ የተፈጸመዉን አስነዋሪ ድርጊት  ከማውገዝ ይልቅ የአገዛዙን የሃሰት ፕሮፓጋንዳ የሚያስተጋቡ ግለሰቦች፣ ሚዲያዎችና የፖለቲካ ድርጅቶችን እያየን መሆኑ ደግሞ እጅግ አሳፋሪ ተግባር ነው ።

የተፈጸመው አሰቃቂ ወንጀል በሃገራችን አንዱ የሌላው መከታና ጠባቂ እንዳይሆንና እርስ በእርስ ለማፋጀትም የተጠነሰሰ ሴራ በመሆኑ ውጤቱ ውሎ አድሮ አደገኛ ወደሆነ ከፍተኛ እልቂት ሊያመራ ስለሚችል እንዲህ አይነት ፍጹም ሃላፊነት የጎደለውን ተግባር ፌደሬሽናችን በጽኑ እያወገዘ

1ኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይና በስሙ የሚነገድበት የኦሮሞ ሕዝብ በተለይ ድርጊቱን እንዲኮንን እና የዐማራን ሕዝብ የህልውና ትግል በመደገፍ  የስርነቀሉ የስርአት ለውጥ  አካል እንዲሆን ጥሪያችንን እናቀርባለን ።

2ኛ ለዚህ ግፈኛ አገዛዝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የወታደራዊ ድጋፍ እያደረጉ ያሉ ሃገራት ተገቢ የሆነ ማጣራት እንዲያደርጉና ለአገዛዙ የሚያደርጉትንም ድጋፍ እንዲያቆሙ አጥብቀን እንጠይቃለን ።

3ኛ  የተፈጸመዉ ወንጀል ገለልተኛ በሆኑ አካላት ተጣርቶ ድርጊቱን የፈጸሙት ወንጀለኞች ባስቸኳይ ለፍርድ ይቀርቡ ዘንድ ፌደሬሽናችን ጥሪዉን ያቀርባል፣ ፣

በድጋሚ በአሰቃቂ ሁኔታ ህይወቱን ለተነጠቀው ወጣት የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን እየገለጽን ለቤተሰቦቹና ዘመዶቹ መጽናናትን እንመኛለን፣

**የአውሮፓ አማራ ማህበራት ፌደሬሽን**


Email: federation@amharaadvocacy.eu / : europeaf2023@gmail.com
https://amharaadvocacy.eu